# የህወሃት አይዲዮሎጂ፣ዶ/ር አቢይና ሕገ መንግስቱ

(ወንድወሰን ተክሉ-ኢትዮሚዲያ አምደኛ)

ሰላም ውድ እድምተኞቼ-እንደምን ሰንብታችኋልሳ?

ከሁሉ አስቀድሜ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለጌታችንና ለመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቴን ከገለጽኩ በኋላ ላለፉት ሁለት ወራት ያህል የጾማችሁትን የሁዳዴ ጾም ዛሬ ቅዳሜ እኩለ ለሊት በኋላና ዶሮ ሲጮህ በሰላም ትፈስኩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፍቃድ ይሁን በማለት ወደ እለቱ አርእስቴ ላመራ እወዳለሁ፡፡

*****

**መነሻ-እንኳን ለአቶ መለስ ራእይ» ስርዓተ ቀብር አበቃችሁ-!

ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በዛሬይታ ታሪካዊትና ቅዱስ እለተ ዓርብ በምድረ ፍልስጥኤም በጸሃፍት ፈሪሳዊያን መሰሪ ሴራና በሮማዊያን አባሪ ተባባሪ ፈጻሚነት ዓለም በአንድ ታላቅ ጻድቅ ላይ በቀራኒዮ የስቅላት እርምጃን የፈጸመች ስትሆን በአንጻሩም በዘረፋና በግድያ ተግባሩ ደግሞ የታወቀን ባርባን የተባለን ነፍሰ ገዳይ በነጻ የለቀቀችበት እለት ነበር፡፡

የዓለም መድሃኒት ጌታችንና መድሃኒታችን ቸሩ መድሃኒያለም በዛሬው እለት በቀራኒዮ ከተሰቀለ በኋላ በቀደምት ነቢያት እንደተነገረው በሶስተኛው ቀን በለተ ቅዳም ሹር ሞትን ድል አድርጎ በተነሳበት ወቅት መጀመሪያ የተገለጸው ለቅድስት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማሪያምና መግደላዊት ማሪያም ነበር፡፡

ሁለቱም ጻድቅ እንስቶች በአንድ ቤት ተሰብስበው በፍርሃት ይርዱ ወደ ነበሩት ደቀመዛሙርቱ ፈጥነው በመሄድ የጌታን ከሞት መነሳት በሚያበስሩበት ወቅት ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ቶማስ የሚባለው «እኔ አላምንም፡፡ በሚስማር የተቸነከሩ እጅና እግሮቹን ዳብሼ ካላየሁ እኔ አላምንም» እያለ ሞግቶ ነበር፡፡

እንስቶቹ የጌታን ትንሳኤ ዜና በሚያበስሩበት ወቅት ጌታ ከመካከላቸው አልተገኘም ነበርና ለቶማስ «እኔ አላምንም» ብሎ እንዲሞግት አድርጎታል ብለን እንገምታለን፡፡ ጊዜና ቦታ እማይወስነው የዓለም መድሃኒት ቸሩ መድሃኒያለምም ድንገት በተዘጋ ቤት ውስጥ እንዴት እንደተገኘ ባልገባቸው ሁኔታ ከመካከላቸው ተከስቶ «ቶማስ ናና እጆችህን በሚስማር በተበሳሱት እጅና እግሮቼ ላይ አስገብተህ ተመልከትና እመን፡፡ ያመን እንጂ ያላመንክ አትሁን» አለው ፡፡

ተጠራጣሪው ደቀመዝሙርም ቶማስ ብርክ ያዘው፡፡ እንደታዘዘውም የጌታውንና የጌታችንን የተቸነከረ እጅና እግር የሚፈትሽበት የሞራል ልእልና አልነበረውምና «ጌታ ሆይ» ሲል የአምላኩንና የአምላካችንን ከሙታን መነሳትን አረጋግጦ ተቀበለ፡፡

የምንኖርበት ዘመን በቶማሳዊያን የተጥለቀለቀበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ባገባደድነው ህማማት ሳምንት መጀመሪያ በእለተ ሰኞ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጧቱ አራት ሰዓት ላይ ላለፉት 26ዓመታት በኢትዮጵያዊያን ላይ ነግሶ የነበረው የመለስ «ራእይ» በይፋ የተቀበረበት ቀን ሲሆን የተቀበረበትም ስፍራ ፓርላማው፤ ገድሎ የቀበረውም አዲሱ ጠ/ም ክብር ዶ/ር አቢይ አህመድ ናቸው፡፡

በእርግጥ እኚህ የ42ዓመቱ ጎልማሳና የሶስት ልጆች አባት የሆኑት አንደበተ ርቱኡ ዶ/ር አቢይ አህመድ በእለቱ የመለስን «ራእይ» ብቻ ሳይሆን የቀበሩት የህወሃትንም የበላይነት ከኢህአዴግ አስኳልነት በመግመስ ሀገሪቷን ሲገዛ ከነበረው ህወሃት መሩ ባለ አንድ እንቁላል ኢህአዴግ ድርጅታዊ ተክለ ቁመና ወደ ባለ ሁለት እንቁላል ሀገር ገዢ ድርጅት አሸጋግረዋል፡፡

ድህረ ዶ/ር አቢይ አህመድ ጠ/ም መሆን ወቅት ኢህአዴግ ህወሃትን አስኳሉ ባደረገ አንድ እንቁላል የሚወከል ሲሆን ከአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር የተጣመረው የቲም ለማ የለውጥ ኋይል ከህወሃት ጋር ተናንቆ በኢህአዴግ ውስጥ ያነበረውን እና በህወሃት ተይዞ የነበረውን የአስኳሉን ስፍራና ሚናን በነጠቀበት ወቅት የነበረው አንዱ እንቁላል ወደ ሁለት እንቁላልነት ሊሸጋገር በቅቷል፡፡

ዛሬ ሀገራችን በጠ/ም ዶ/ር አቢይ የሚመራው የቲም ለማ ቡድን አስኳልነት አንድ ገዢ ኢህአዴግ የተባለ እንቁላልና በአንጻሩም ህወሃትን አስኳሉ ባደረገ ሁለተኛ የኢህአዴግ እንቁላል (ሁለት ጉልበት ያላቸው ገዢ ኋይሎች) ተፈጥረው የምታስተናግድበት ወቅት ሆኗል፡፡

ስለ መለስ «ራእይ» ስርዓተ ቀብር መፈጸምና የህወሃት የበላይነት በአንደኛው የኢህአዴግ እንቁላል ውስጥ ማክተም እንደ የጌታችን ደቀ መዝሙሩ ቶማስ ሳላይ አላምንም የምትሉ ኢትዮጵያዊያን ቶማሶች (በተለይ በተለይ ዲያስፖራው)የምላችሁ ነገር ቢኖር እውነት እውነት እላችኋለሁ «ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን ናቸው» የሚለውን የጌታን ህያውና ዘላለማዊ ቅዱስ መልስ ነው የምሰጣችሁ፡፡

ለመሆኑ በህይወት ዘመናችን ማንኛቸውንም ነገር አይተን፣ፈትሽንና መርምረን መኖራቸውን ካረጋገጥናቸው ክስተቶችና ኩነቶች ይልቅ ሳናይ፣ሳንመረምርና ሳንዳብስ ግን መኖራቸውን አምነን የተቀበልናቸው ኩነትና ክስተቶች እጅግ በለጠው እንደሚገኙ ያውቃሉን?

ክብር ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድ የጠ/ምኒስትርነቱን ስልጣን በይፋ በተረከቡበት ወቅት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቴሌቪዢንና በራዲዮ በቀጥታ በተላለፈ 35 ደቂቃ በፈጀው ታሪካዊው ድንቅ ንግግራቸው  የማቹን አቶ መለስን «ራእይ» ቀደም ብለው ያቆሳሰሉትን እስትንፋሱን ሲጥ አድርገው በመግደል ለመካነ መቃብር ያበቁ ጀግና መሪ ናቸው፡፡

ያለ አንዳች ጥርጥርና መነታረክ የአቶ መለስ ህወሃታዊ አይዲኦሎጂና «ራእይ» ከሁለት ዓመት ጀምሮ ሲገዘገዝ እና በህዝባዊው ትግል ጦርና ጎራዴ ሲቆራረጥና ሲጠቀጠቅ ከርሞ በ2018 ላይ በዶ/ር አቢይ የመጨረሻ ጥይት ህልፈቱ ተፈጽሞ ለመቀበር በቅቷል፡፡

ግን የህወሃት አይዲኦሎጂያዊ መንፈስ ወይም የአቶ መለስ «ራእይ» ድብን ብሎ የሞተና ብሎም የተቀበረ ቢሆንም የድርጅቱ ሰንኮፍ ወታደራዊ፣ኢኮኖሚያዊና የደህንነት ተቋማትን ይዞ «ህልውናዬ ዛሬም ቢሆን አለ» በማለት እየተግደረደረና ብሎም «ነፍስ ዘርቼ እነሳለሁ» በማለት እራሱን ለተግደርዳሪ ተግባር እያዘጋጀ እንዳለ የማይካድ እውነታ ነው፡፡

ይህን እውነታ የማመን እና ያለማመን ውሳኔ ለእናንተው የተተወ ሆኖ ሳለ የእናንተ አለማመን በሀገራችን የተፈጠረውን ተጨባጭ እውነታ ባለማወቅ የምትወጡትን ሚና እንዳትወጡ ከማገድ ባሻገር የሚያመጣላችሁ አንዳችም ጥቅም እንደሌለ ግን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

እንግዲህ ጸሓፍት ፈሪሳዊያንና ሮማዊያን እንደ ነፍሰ ገዳይ ወንጀለኛ በመቁጠር ስቅላት ፈርደውበት በዛሬው ቅዱስ እለተ ዓርብ በቀራኒዮ የሰቀሉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይነሳል ብለው ላላመኑት፣ይነሳል ብለው ላልጠበቁትና እና ትንቢቱ ተገልጾላቸውም ትንሳኤውን ለጠበቁት በሶስተኛው ቀን ከሙታን እንደተነሳ እና ሞትንም ድል እንዳደረገ የአቶ መለስ «ራእይ» ህልፈተ

ህይወት ተፈጽሞ ከተቀበረ በኋላ የራእዩ ተሸካሚ ሶንኮፉ ብቻ ከቀረ እነሆ አምስተኛ ቀናችን መሆኑን እወቁ ብል ይህ ጸሃፊ እንዴት ቢዳፈር ነው የምትሉ ትኖራላችሁ ብዬ አልገምትም፡፡ (የማቹ ራእይ ተጠቃሚዎችና አራማጆች በእርግጥ ይህን ዜና አሁን ባለንበት ደረጃ ተቀብለው ማጣጣም እጅግ እንደሚከብዳቸው በሚገባ እረዳለሁ)

ጸሓፊው ይህን መሰል መደምደሚያ ላይ እንዲሁ በግል ፍላጎትና ምኞት ላይ ተመርኩዞ የተናገረው የዘፈቀደ ግምት ሳይሆን ላለፉት ሶስትና አራት ወራት ያህል ስለ ህዝባዊው ትግል ወለድ ስለሆነው በገዢው ኢህአዴግ ውስጥ ስለተፈጠረው አዲስ የለውጥ ኋይል ቀደም ብሎ በዝርዝር (ለምሳሌ «የኦህዴድ ቦልሼቪክና ግላስኖትስ»..«የመጨረሻው ካርድ ወታደራዊ አገዛዝ?»..«የአቶ ለማ መገርሳ መንገድ.» እና ወዘተ በመሳሰሉት አርእስቶች ስር ወደ ዛሬ ክስተት የሚያመራን ድርጊቶች መፈጸማቸውንና መታቀዳቸውን የገለጽኩበትን ለአብነት መጥቀስ ይቻለኛል)ሳቀርብ የነበረና ባለኝ ግልጽና ተጨባጭ የውስጥ መረጃ መሰረት ዛሬ ከቶም አዲስ ያልሆነ ግን የለውጥ ኋይሉ የቲም ለማ ቡድን የዓመት ከመንፈቅ የስራ ውጤት አንጻር እንጂ የማየው እንደ ዱብ እዳ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡

በነሀሴ እና መስከረም 2017 ወራቶች ውስጥ ስለ ቲም ለማ በኢህአዴግ ውስጥ የበቀለ ልዩ የለውጥ ኋይል መሆኑን በምዘግብበት ወቅት አብዛኛው አንባቢ በተቃራኒ መንገድ የእነ አቶ ለማን እንቅስቃሴ በህወሃት በጎፈቃድ እየተፈጸመ ያለ ድራማ ነው በሚል እምነትና አቋም የጸና የነበረ ሲሆን ቁጥሩ እጅግ ቢቀንስም ዛሬም አይደለም የአቶ መለስ «ራእይ»ተገድሎ መቀበር ይቅርና እነዚህን ውስጣዊ የለውጥ ኋይሎችን የህወሃት አገልጋይ ቅጥረኛ ብሎ የሚያይም እንዳለ አውቃለሁ፡፡

መርምሩ ታውቁ ዘንድ-እመኑ ባታዩም የሚለውን የጠቢቡን ብሂል በመዋስ የቲም ለማን መራሹን የለውጥ ኋይል በጥልቀትና በቅርበት ለመከታተል ከሞከርን የሚታየን እውነታ ቀደም ሲል በአእምሮዋችን ከሳልነውና አምነን ካስቀመጥነው እውነታ ሲጣረስብን በግልጽ ማየት ይቻለናል፡፡

በነገራችን ላይ አንጋፋው የታሪክ ምሁር፣አክቲቪስትና ፖለቲከኛ በሆኑት ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም «ላለፉት አርባ ዓመታት ሰምቼው አማላውቀው ድንቅና ጠንካራ ንግግር » የተባለውና በታሪካችን ለመጀመሪያ ግዜ አጠቃላይ የተቃዋሚውን ጎራ (ከኦነግ በስተቀር)ድጋፍና ተቀባይነትን ያገኘው የጠ/ምኒስትሩ ታሪካዊ ተስፋ ሰጪ ንግግር በይዘቱ ሳይሆን በቀረበበት የስልጣን ደረጃ እንደ አዲስ ሆኖ ያስደሰተኝ ቢሆንም በይዘቱ ግን ምንም አዲስ ያልሆነና በእነ አቶ ለማ መገርሳ፣ዶ/ር አቢይ አህመድ፣አቶ አዲሱ አረጋ፣አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፣አቶ ጥላሁን ንጉሱ ላለፉት አስራ ሁለት ወራቶች ውስጥ በተለያየ መድረክና ስፍራ ሲነገሩ የነበሩ የለውጥ ፈላጊው ኋይል እምነትና አቋሞች መሆናቸውን በሚገባ አስታውሳለሁ፡፡

ሁለተኛ እንኳን ከአቶ መለሱ ዘመነ ከፋፍለህ ግዛ ወደ ተከበሩት ጠ/ም ዶ/ር በአንድነትና እኩልነት መርህ ግዛ ዘመነ በሰላም አደረሳችሁ፡፡

ዶ/ር አቢይ አህመድ 35 ደቂቃ በፈጀው ታሪካዊ ንግግራቸው (ንግግሩ የዶ/ሩ ግለ ፍላጎትና ዓላማ ሳይሆን በአጠቃላይ የቲም ለማ ተብሎ የሚጠራው የለውጥ ኋይሉ የጋራ መተዳደሪያና መመሪያ ማንፌስቶ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማስገንዘብ እውዳለሁ)እሳቸውን በመሪነት የመረጠው የቲም ለማ የለውጥ ኋይል ከህወሃቱ አይዲኦሎጂ ጋር በፍጹም በማይገናኝ መልኩ ተፈጥሮአዊ ነጻነት፣የህግ የበላይነት የሰፈነበት ፍትሃዊ አስተዳደር፣በስልጣን ያለአግባብ መባለግ በህግ የሚዳኝበት፣ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተስፋፍቶ መንግስት የህዝብ አገልጋይ የሚሆንበትን እና ብሎም እድሜ ጠገብ የኢትዮጵያ ታሪክን ያከበረ ኢትዮጵያዊ አንድነትን አስኳሉ ያደረገን አስተዳደር ያስተዋወቁን ሲሆን ከህወሃት አይዲኦሎጂና አላማ ጋር የሚጣረሱ አዲስ መንገድ እንደጀመርን አብስሮናል፡፡

ማን ነበር «እያንዳንዱ ስርዓት የሚተካውን አዲስ የስርዓት ጽንስ የጸነሰ ነው» ያለው ? ሌኒን ሳይሆን አይቀርም፡፡ በኢህአዴግ ውስጥ ለተካሄደ የስልጣን ሽግሽግ «እንዴት የለውጥ ሂደት ተደርጎ ይገለጻል »እና «የሚፈለገው ስር ነቀል ለውጥ እንጂ እዚያው በኢህአዴግ ውስጥ ከአቶ ኃይለማሪያም ወደ ዶ/ር አቢይ በማዘዋወር የታየ ለውጥ የለም» ለምትሉ ወገኖች የስርነቀል ለውጡን አይነት በአጭሩ ለማስቀመጥ እወዳለሁ፡፡

በሀገራችን ተደጋግሞ የተከሰተውና በተቀረውም ዓለም ሲከሰት ያየነው ሁለት ዓይነት ስርነቀል ለውጥ ሂደቶችን ሲሆን ውስጣዊና ውጪያዊ የለውጥ ኋይሎች እንደፈጸሙት እናያለን፡፡ በ1960ዎቹ አጋማሽ የተነሳው ህዝባዊ ዓመጽ ከዓመታት ግብግብና መስዋእትነት በሃላ የስርዓቱ አገልጋይ የነበረው መከላከያ ወደ ህዝቡ በመቀላቀልና ህዝባዊውን ጥያቄ በማንገብ ሲያገለግለው የነበረውን ስርዓት አፈራርሶ አዲስ ስርዓት(በወቅቱ ስለተቋቋመው የስርዓት ቅርጽና ይዘት አይደለም እየገለጽኩ ያለሁት)ያቋቋመብትን ክስተት እንደ የውስጣዊ ኋይል የለውጥ ዓይነት አድርገን እንወሳዳለን፡፡
በአንጻሩም የውጫዊ የለውጥ ኋይል ብለን የምንገልጸው በ1983 በህወሃት መራሹ የተመራው የታጠቀ ሽፍታ ኋይል በመሳሪያ አፈሙዝ ስርነቀል ለውጥ የመጣበትን ክስተት መጥቀስ ይቻለናል፡፡

ዘንድሮ ያለንበት የለውጥ ሂደት የ0960ዎቹ አይነት በውስጣዊ የለውጥ ኋይል የሚፈለገውን ስርነቀል ለውጥ ለማምጣት እነሆ ወሳኙን ድል መጎናጸፍ ተችሏል ቀሪውን ሁለንተናዊው ድል ለመጎናጸፍ ታራካዊ ምእራፍ ላይ እንገኛለን፡፡

**የህወሃት አይዲኦሎጂ፣ዶ/ር አቢይና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት-

የአቶ መለስን ከፋፍለህ ግዛ እና የስልጣንን ማእከላዊነት ያጸና አገዛዝን በመንግስት ህዝብን አገልጋይነትና የሀሳብ ልዩነትን እንደ የሀገሪቱ እድገት መሰረት አድርጎ የተነሳን አይዲኦሎጂ የተካው የጠ/ምኒስትሩ ንግግር ወደ ተግባር ከማምራቱ በፊት በብርሃን ፍጥነት ህወሃት በአቶ ሺፈራው ሺጉጤ በኩል በእለቱ (ሰኞ ማለቴ ነው) «የኢህአዴግ አሰራር ቡድናዊ የጋራ ስራ እንጂ በጠ/ም/ሩ ብቻ የሚሰራ አይደለም » በማለት የጠ/ምኒስትርን ስልጣን እንደ ስልጣን አልባ አድርጎ ለማቅርብ ሲውተረተር ስምተናል፡፡

ለምንድነው በእንደዚያ አይነት ፍጥነት ስለ ኢህአዴግ ድርጅታዊ የቡድን ሰሪነት ሊነግሩን የፈለጉት፡፡

በእርግጥ ድርጅቱ ላለፉት 26ዓመታት በድርጅታዊ ቡድን ሀገሪቷን እየገዛ የነበረ ነውን?

ይህ ድርጅታዊ ማእከላዊነት እየተባለ የሚገለጸው የኢህአዴግ አሰራርና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከሕገ መንግስቱ ጋር የተጣጣሙ ናቸውን?

አሁን በኢህአዴግ ውስጥ የቀረውና ወታደራዊውን ክፍል የያዘው የህወሃት ሰንኮፍ የጠ/ም ዶ/ር አቢይና የለውጥ አራማጁን ውስጣዊ ኋይልን የለውጥ ፕላን ለማከሽፍ በጦሩና በደህንነቱ ከመጠቀም ይልቅ በቅድሚያ የሚመርጠው ማጥቂያ መንገድ ይህ ድርጅታዊ ማእከላዊነትን ያቀፈ የቡድን አሰራር እንደሆነ ይገመታል፡፡

የኢህአዴግ ማእከላዊነትን የጠበቀ ድርጅታዊ የቡድን አሰራር እስከ 1993ቱ የህወሃት መሰንጠቅ ድረስ የነበረ አሰራር ቢሆንም ከሕገ መንግስቱ ጋር ግን በፍጹም ሳይጣጣም በተጣረሰ መልኩ ሲፈጸም እንደነበረ መታወስ አለበት፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሃራምባ እና ቆቦ ወይም ውሃና ዘይት የሆኑ ያህል የማይጣጣሙና የሚጣረሱ ሆነው ሳለ ኢሕገ መንግስታዊ ስልጣን፣ኢኮኖሚና ማህበራዊ የበላይነትንና ጥቅምን በመገንባቱ የሚታወቀው ህወሃት ያው «ጠያቂዬ ማነው» በሚል በማን አለብኝነት ሲጠቀምበት መክረሙን እንረዳለን እንጂ በሕገ መንግስቱ የተደገፈ አሰራር እንደዘረጋ አይደለም የምንረዳው፡፡

በሕገ መንግስቱ የተፈቀደው ግን ያልተተገበረው የጥምር ፖለቲካ ስርዓት፣የሀሳብ ነጻነት መከበር፣ የመጻፍ፣የመናገር፣የመደራጀትና ብሎም የመምረጥ፣መመረጥና የመቃወም መብቶች በይዘታቸው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና ጋር እሳትና ጭድ የሆኑ ሆነው ሳለ አቶ መለስ ግን ለዓለም ሀገሪቷ የምትገዛው በሕገ መንግስቱ ግን በተግባር በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማሌሊት ፍልስፍና ፋሺስታዊ ስርዓት ሲገዛን መቆየቱ ይታወቃል፡፡

እንደ ሕገ መንግስቱ ከሆነ ማንኛውም ሕግ ከሕገ መንግስቱ ጋር በማይቃረን መልኩ መውጣት አለበት ሲልም ይደነግጋል፡፡ ያ ማለት የኢህአዴግ ድርጅታዊ ማእከላዊነትን ያጠበቀ የቡድን ስራ ምንም እንኳን ህወሃት ለሁለት እስኪሰነጠቅ ቢጠቀምበትምና ብሎም ዛሬም መልሼ እጠቀምበታለሁ ብሎ ቢቋምጥም ህጋዊ መሰረት የሌለው ከመሆኑ አንጻር ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው እየተንቀሳቀሱ ላሉት የእነ ቲም ለማ የለውጥ ኋይሎች ሊያገለግል እንደማይችል ያውቁታል፡፡

በሚደንቅ ሁኔታ የህወሃትን ቀልብ ገፎ የአቶ መለስን «ራእይ » የቀበረው የሰኞ እለቱ የጠ/ም ዶ/ር አቢይ ታሪካዊ ንግግር ሕገ መንግስታዊ መሰረት ያለው ሆኖ መገኘቱ ሲሆኑ ይህንኑ የህወሃትን ድርጅታዊ ማእከላዊነትን የጠበቀ ቡድናዊ አሰራርን የማስፈን ሴራን በሕገ መንግስቱ ላይ ተመርኩዘው ፍርስርሱን እንደሚያወጡትና እንደምናወጠው ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እየተካሄደበት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አዲሱ ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አቢይ አህመድ በህወሃት በኩል እንደ የመጽሃፍ ቅዱስ ቃል የሚታመነውን ተቃዋሚን ሁሉ «ጸረ ሰላም ኋይሎች፣ይህዝብ ጠላቶችና አሸባሪዎች» ብሎ የመፈረጅን ሰይጣናዊ ሴራን አክሽፈው ተቃዋሚውን ለሀገር እድገት የሚጠቅም ተፎካካሪ ሲሉ በመፈረጅ ለተቃዋሚው ሁሉ የአብረን እንስራ ጥሪን አስተላልፈዋል
፡፡

አቶ ለማ መገርሳ እንዳሉት «ይህ ድል የተገኘው በከባድ ትንቅንቅና ትግል ነው» ያሉ ሲሆን አክለውም «ከዚህ በኋላ የሚቀረው እጅግ ወሳኝና ትልቅ ፈተና ስለሆነ ህዝቡ ድሉን ሁለንተናዊ ለማድረግ መታገልና ዶ/ር አቢይን መደገፍ አለበት» ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የተነሱት ውስጣዊ የለውጥ ኋይሎች በህዝባዊው ትግል ከባድ መስዋእትነት የዛሬን መንግስታዊ ስልጣን መጨበጥ ቢችሉም ወታደራዊ ተቋሙን የተቆጣጠረው የህወሃት ሰንኮፍ እስካልተነቀለ ድረስ የህዝባዊው ትግል ዶ/ር አቢይን ባካተተ መልኩ ሳይቋረጥ ተጧጡፎ መቀጠል ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ግን ዓይኖች ሁሉ ወደ ዶ/ር አቢይ ያያሉ-ጆሮዎች ሁሉ ከዶ/ር አቢይ ድምጽ ለመስማት ይጠባበቃሉ-የህዝባዊው ትግል ልጅ የሆኑት ክቡር ጠ/ምኒስትሩም ቃል የገቡትን ህዝባዊ ተስፋ ለመተግበር ለስልጣን ያበቃቸውን የህዝባዊውን ድጋፍ ድምጽ ለመስማት ይጠብቃሉ፡፡

በእስካሁኑ ቅንጅታዊ ትግል ህዝባዊው ትግል የቲም ለማን የለውጥ ኋይል ይዞ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ
ከደረሰ ቀጣዩ የትግል እስትራቴጂም በተመሳሳይ መልሉ መንግስታዊውን የመሪነት ስልጣን ይዞ በመታገል ሁለንተናዊውን የለውጥ ድል ይጎናጸፋል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ለዚህ ደግሞ እርሰበርስ መናበብና እርሰበርስ እውቅና መሰጣጣት የቅድሚያ ተግባር ነው፡፡
ይህ የዶ/ር አቢይ አህመድ ጠ/ምኒስትርነት ስልጣን የህዝባዊው ትግል ድልና (ግማሽ)ውጤት መሆኑን በመቀበል መጀመር ያስፈልጋል፡፡
መልካም የትንሳኤ በአል ለሁላችሁ፡፡ ቸር እንሰንብት!